# <u>አሚሚቷን ብትመርጥ</u>

ወያኔ ተናግታ ፤ ከስር ተነቃንቃ
ዙሪያው ጨልሞባት ፤ ተይዛ በሲቃ
ጉድጓድ ተምሶላት ፤ ተፈንግላ ወድቃ
አይን ምስክር ነው ፤ ስታላቁጥ ጭቃ
ፍዳዋን ታያለች ፤ ላትጨርሰው ዝቃ
ነገ ለምትሞተው ፤ ተተብትባ ታንቃ ።

በየቦታው ቢሮጥ ፤ ቢባልም ተፍ ተፍ
ሰላይ አሰማርቶ ፤ ወሬ ቢነፈነፍ
አዋጁ ቢንጋጋ ፤ ወታደር ቢሰለፍ
ወያኔ የሚሏት ፤ መዥገር ሳትቀረፍ
ከግባችን ሳንደርስ ፤ አልሞ መጨንገፍ
መች ይታሰብና ፤ ሳይጨርሱ ማረፍ
ከንቱ መንፈራገጥ ፤ ከሞት ላይተረፍ ።

ምንም ቢያዳክማት ፤ ትግል በፈረቃ
ሱሪዋ ቢረጥብም ፤ ፈርታ ተንቦቅቡቃ
እንዳታንሰራራ ፤ አሙቿ ጠብቃ
ስብርብሯ ወጥቶ ፤ እንዳሸዋ ደቃ
ትንፋሽ እንዳታገኝ ፤ ወያኔ ትወቃ!
የባንዳዋን ዘመን ፤ እንዝጋው አበቃ ።

የፈረንጆች ሎሌ ፤ የአረቦች ቡቺ
እንደፌንጣ ብትዘይ ፤ ከበሮ ብትመቺ
የሱዳኑን ጠንቋይ ፤ ሰይጣን ብትጎትቺ
ዘንድሮን አታልፊም ፤ አይቀርም ሳትሞቺ
ወይዘሮ ወያኔ ፤ ይልቅ መላ ምቺ
ሺ ቦታ ከመሮጥ ፤ የሚበጀው ላንቺ
እንጦሮንጦስ ግቢ ፤ ሰው ስራ አታስፈቺ ።

አይቀሬው ሞት ሲደርስ ፤ ያለ ነው መደንገጥ
ግድግዳ መጫሩ ፤ ግድግዳ መቧጠጥ
አልሞትኩም ለማለት ፤ መደንፋት ማንዛረጥ
ሺውን መቀባጠር ፤ ከሞት ላይመለጥ
የሟች ወግ ነውና ፤ ጣር ላይ መንፈራገጥ
መቼም አንፈርድባት ፤ ብትልም ዘጥ ዘጥ
በተሻላት ነበር ፤ አሚሚቷን ብትመርጥ ።

ታዛቢው

March 2, 2018